በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል የቀረበ ሳምንታዊ ትንተና

ሰኔ 4 ቀን 2015 ዓም(25-06-2023)

## በከፈሉት መጠን መከፈል፣በሰፈሩት ቁናም መሰፈር አይቀርም!

ለከፉም ሆነ ለመልካም ውጤት የሚከፈል ዋጋ አለ።በከፈሉት ዋጋ መጠን የግልባጭ እኩል ውጤት ወይም ምላሽ እንደሚኖር እንግሊዛዊው የስሌትና የፊዚክስ ሊቁ አይዛክ ኒውቶን ስለ እንቅስቃሴና ግፊት ባቀረበው ሳይንሳዊ ትንተና ሦስተኛ ሕግ አድርጎ ባቀረበው ሃሳቡ እንዲህ ሲል ያስቀምጠዋል፤"For Every action ,there is an equal and opposite Reaction"።ይህንን ሁለእንተናዊ ሳይንሳዊ ሕግ በህብረተሰብ እንቅስቃሴ ወይም ህይወት ላይ አስቀምጠን ብናዬው፣ የሚከተለውን ይመስላል። ለተወሰነ ጊዜ ጥቅም ሲሉ በአድርባይነት ከአምባገነኖችና ከዘረኞች ጎን በመቆም በሌሎች ላይ ግፍ ቢሰሩ፣ ወይም በፍርሃት ክፉ አድራጊዎችን ሳይቃወሙ በዝምታና ግዴለሽነት መልክ ቢቀመጡ የሚገኘው ውጤት የተገላቢጦሽ ይሆንና ሌላውን ለመጉዳት ብቻም ሳይሆን እራስን ለባርነት የሚዳርግና በመጨረሻም የራስን መቃብር ለመቆፈር የሚከፈል ዋጋ ይሆናል።በሌላም በኩል ግፈኞችን ተቃውሞ ለሰብአዊ ክብር፣ለእኩልነት፣ ለአገር ነጻነትና አንድነት በቆራጥነት መታገልና የሚያስፈልገውን መስዋእትነት መክፈል ደግሞ በአሃዝ የማይተመን ክብር ላለው ምክንያት የሚከፈል ዋጋ ሲሆን ውጤቱም የግፈኞችን ስርዓት በማስገድ ፍትሓዊ ስርዓት እንዲሰፍን ያደርጋል።ይህ የሁለቱም እንቅስቃሴ ተቃራኒ ውጤት ያመጣል የሚለውን አገላለጽ ትክክለኛነት ያረጋግጥልናል።ፋሽስቶች ለሚፈጽሙት እንቅስቃሴ ጸረ ፋሽስት እንቅስቃሴ መውለዱን ፣ለጎሰኞች ጸረ ጎሰኞች፣ለአገር አፍራሾች ጸረ አገር አፍራሽ የሆነ የአገር ወዳዶች ትግል መፈጠር ምክንያት እንደሚሆንና ለአንዱ ጉዳት ለሌላው ጥቅም የሆነ ውጤት በመፍጠር በኒውተን ሳይንሳዊ ቅምር የሚጠናቀቅ ይሆናል።

የሰው ልጅ ኑሮውን ለማሻሻል ሲል ትግል ያደረገው ገና ከጅምሩ ነው። ለመኖር መብላትና መጠጣት ስላለበት ያንን ለማግኘት በሚችለው መንገድ ጥረት አድርጓል።የተፈጥሮን ከባድ ሸክም ለማቃለል ሲል ብዙ ውጣ ውረዶችን ተጉዟል። የተፈጥሮን ጫና ለማቃለል በሚያደርገው ትግል ውስጥ ሆኖ በውስጡ በተነሳ የጥቅም ግጭት ውስጥ ገብቷል።አንዱ የሌላውን መብትና ጥቅም ለመንጠቅ ፣ሌላውም ላለማስነጠቅ በተነሳው የእርስበርስ ሽኩቻም የመሸነፍና የማሸነፍ ውጤቶች ተከስተዋል፣ውጤቱ የሚወሰነው በአቅም

ጥንካሬ መሆኑም ታይቶበታል። በመሸናነፍ ጉዞ የቀጠለው የሰው ልጅ አሁንም ቢሆን ከእርስ በርስ ግጭትና ጦርነት አልወጣም። ከተፈጥሮ ጋር ከሚያደርገው ትግል ይበልጥ ሃይሉን የጨረሰው ከራሱ ጋር ባደረገው ትግል ነው።ለሰው ልጆች በጎ ጥቅም ሊውል የሚገባው እውቀትና ሃብት ለሰው ልጆች እልቂትና መከራ ውሏል፤አሁንም እዬዋለ ነው።አገራትን መውረር፣ህይወትም ተፈጥሮንም ባጠቃላይ የሚያወድም እስከ ኑክሌር የጦር መሳሪያ የመስራቱ፣የበሽታ ባክቴሪያ እያዳቀሉ መበተን የራስ ወዳዶችና የቀማኞች ሙያ ከሆነ ውሎ አድሯል።በዚህ የዓለም ንጹሃን ሕዝብ ለመከራና ለእልቂት ተዳርጓል፣ከጦርነት ሳይወጣና የሰላም አዬር ሳይተነፍስ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሷል።ጊዜ በተለወጠ ቁጥር የሰውም ልጅ ፍላጎቱ እዬተለወጠ ፣የግጭቱም አይነትና መጠን ፣የጦር መሳሪያውም ብዛትና ጉልበት እዬተቀዬረ መጥቷል።ዓለም በሁለት ጎራ ተከፍላ የሞት የሽረት ትግል የሚካሄድባት የስጋትና የእልቂት መድረክ ሆናለች።

የእራስ ወዳዶች ፣የወራሪዎችና የዘራፊዎች ጎራና፣ ለሰው ልጆች ክብር፣ ሙብትና እኩልነት የተሰለፉበት ጎራ ሆናለች ።በነዚህ ጎራዎች ውስጥ የተሰለፉ ሃይሎች በሚሰሩት ሥራና በተሰለፉበት ዓላማ አንጻር የሚገለጹበት ጸባይና ስያሜ አላቸው።ድርጊታቸውም እንዲሁ።

በወራሪነት፣በዘራፊነት የተሰለፉት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴና ለሚፈጽሙት ወንጀል ብዙ መሸፈኛ ዘዴዎች አሏቸው።ከቶም ቢሆን እራሳቸውን ወንጀለኛ አድርገው አያቀርቡም።በነሱ እይታ ለነሱ ፍላጎት ያልቆመውና የሚቃወማቸው ወንጀለኛ ነው።ተቃዋሚውን ለማሸነፍ ከሚያደርጉት የጭካኔ እርምጃ ጎን ለጎን ለጥቅም ያደሩትን ሆድ አደሮች በማሰለፍ በተቃዋሚው ላይ ያዘምቱበታል።ይህ አድርባይ ቡድን በመሰለል፣ውዥንብር በመንዛት፣በመጠቆምና መንገድ በመምራት ከሚያበረክተው የባንዳነት ተግባር በተጨማሪ ለመለመሉት ክፍሎች ጠበቃና ደጋፊ በመሆን ያገለግላል።በዚህ አድራጎት ላይ የተሰለፈ ከንቱ በዓለም ሕዝብ ግንዛቤ የቁም ሙት(the living corpse)ተብሎ ይመደባል።በመንፈስ ቀድሞ ቢሞትም በስጋውም አሟሟቱ አያምርም፤ሲኖር እንደ ውሻ ሲሞትም እንደውሻ ነው።በተቃራኒ ጎራ ለሰው ልጆች ጥቅም፣ለአገር ክብር ሲሉ የሚሰለፉ ጀግኖች ቢሞቱም ሰማእታት ተብለው ይመደባሉ።

በእኛም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለአገር አንድነት፣ነጻነት፣ብሔራዊ ክብር፣ለፍትሕና ለእኩልነት መሞት በታሪክ የሚያስወድስ የጀግንነት ተግባር እንደሆነ ይታመንበታል።ሁለት አይነት አሟሟትም ስላለ አሟሟቴን አሳምርልኝ የሚባለው ተማጽኖ ባርነትን ተቀብሎ በቁሙ ሞቶ ከመኖር እምቢ አልገዛም ብሎ በመንፈስ ሳይሆን በስጋ መሞት እንደሚመረጥ የሚያሳይ ነው።

በአገራችን ታሪካዊ ጉዞ ለነዚህ ሁለት ጎራ ግብአቶች ዜጎች ዋጋ ከፍለዋል።የዜጎች ዋጋ ባይጨመርበት ኖሮ ሁለቱም ግብአቶች መከሰታቸው ቀርቶ መታሰባቸውም ባልተቻለ ነበር።ለአገራችን ነጻነትና አንድነት ዜጎች የህይወት ዋጋ እንደከፈሉት ሁሉ በተመሳሳይም ለሰፈኑት ስርዓቶች ዕድሜ መርዘም እንዲሁ ዜጎች ዋጋ ከፍለዋል።

ለዘውዳዊ ስርዓትና ለባላባታዊው አገዛዝ በደጋፊና በተቃዋሚ በኩል ብዙ ዋጋዎች ተከፍለዋል።በዚያም ምክንያት ነው ሥርአቱ ለመኖርና ለመገርሰስ የበቃው።ሃይሉ በተጠናከረ መጠን የአንዱ የበላይነት ገዝፎ ይወጣል።ሃይሉ በጫጨና በኮሰሰም ጊዜ ይፍረከረክና ይወገዳል።ለዘመናት የቆዬው ባላባታዊ የዘውድ ስርዓትም ከዚህ የታሪክ ጉዞ ሊያመልጥ አልቻለም።ጊዜው ሲደርስና የተቃዋሚው ጎራ ሲጠነክር ቦታውን ለመልቀቅ ችሏል።ምንም እንኳን ከዘውዳዊ ባላባታዊ ስርዓት መገላገሉ አንድ የለውጥ ሂደት ቢሆንም ሕዝቡ የፈለገውንና ብዙ መስዋእት የከፈለለትን እውነተኛ ለውጥ ለማግኘት አልቻለም።የሕዝቡ ትግል በሌሎች አምባገነኖች ተጠልፎ ለሌላ የባርነትና የጭቆና አገዛዝ ተዳረገ እንጂ መሰረታዊ ለውጥ አልመጣለትም።ያም ሊሆን የቻለው በጥፋት ሃይሉ ዙሪያ ለተገነባው ሃይልና ጎራ ለጥቅም እራሱን የሸጠ፣ የፍርሃትና የአድርባይነት ዋጋ የከፈለ ሕዝብ በመኖሩ ነው።

ላለፉት 50 ዓመታት ለሰፈኑት አምባገነናዊና ጎሰኛ ስርዓቶች ዕድሉን የሰጠ ዋጋ ተከፍሏል።ፍርሃት፣አድርባይነት፣ጎሰኝነትና ኃላቀርነት ከሚጠቀሱት ዋናዋናዎቹ ናቸው።ከአምባገነኖችና ከጎሰኞችም ለመላቀቅና እውነተኛና ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ብዙ ትግልና የህይወት ዋጋ ተከፍሏል፤አሁንም እዬተከፈለ ነው። በሁለቱም ጎራዎች የሞት የሽረት ትግል በመካሄድ ላይ ነው።የትግሉ ሂደት እንደሚያሳዬው ከሆነ ላለፉት 32 ዓመታት በወያኔ ግንባር ቀደምነት ኢሕአዴግ በሚል ጭንብል ሰፍኖ የቆዬው የጎሰኞች ስርዓት በአድር ባይና ጎሰኞች ተሳትፎ ለመቆዬት ቢችልም ፣ በተፈጥሮ ሕግ ሁሉም ነገር ዘለዓለማዊ ሆኖ እንደማይኖርና በያዘው መንገድ እንደማይቀጥል ፣በውስጣዊና ውጫዊ በሆነ የለውጥ ሂደት እንደሚናጥ በሳይንስ የተረጋገጠውን የእድገትና ውድቀት የለውጥ ግዴታ ተከትሎ ሊቀጥልበት ባለመቻሉ የራሱ ውስጣዊ አካል በሆነው ኦሕዴድ በተባለው ሊቀዬር ችሏል። ባለፉት 5 ዓመታት የጎሰኛ ስርዓቱን የሚመራው ይህ የኦሮሙማው ተረኛ ቡድን ብልጽግና በሚል ጭንብል ተከሽፎ ከወያኔ ውድቀት ተምሮ ለባሰ ወንጀልና ዘረኛ ግፎች ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን የሁሉንም ጸረ ሕዝብ ስርዓቶች ያስናቀ ሆኗል።

የለውጥ ሂደት የነበረ፣ያለና የሚኖር በመሆኑ የዚህም ፋሽስታዊ ጸረ ሰው፣ጸረ አንድነት፣ጸረ ፍትሕ የሆነ ስርዓት መውደቂያው እንደማይቀር እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል። አሁንም ዓይን ያወጣው ዘረፋ፣ ገደብ የለሽ ወረራውና ማፈናቀሉ፣የአረመኔነቱ መጠን በጨመረ ቁጥር የሚቀበርበትን ጉድጓድ እዬቆፈረ መምጣቱን ያፋጥነው እንደሆነ እንጂ ለዘለዓለሙ በሥልጣኑ ላይ የሚያቆዬው እንደማይሆን እርግጠኞች ነን።አንዳንድ ምልክቶችም እዬታዩ መጥተዋል።የተቃዋሚው ጎራ እያደገ በመምጣቱ የራሱ ተባባሪዎች ሳይቀሩ ድንጋጤና ብርክ ውስጥ በመግባት ከድጋፍ ወደ ተቃውሞ የገቡበት ሁኔታ በመታዬት ላይ ነው።ይዋል ይደር እንጂ የመውደቂያው ጊዜ የተቃረበ ይመስላል፤ከቶም ቢሆን በያዘው የአፈና፣የጥላቻ፣የመከፋፈል፣የዘረፋና የአገር ክህደት ተግባር ለዘመናት ይቀጥላል ተብሎ አይታሰብም፤እንዳለፉት ስርዓቶች ሁሉ የታሪክ አሳፋሪ ገጽ ይዞ መቀመጡ አይቀሬ ነው።

ለመጨረሻው ውድቀቱ በስህተትም ሆነ በፍርሃት ወይም በጥቅም በውስጡ የተሰበሰበው አድርባይ ሰፈሩን እዬለቀቀ በመውጣት ከዚህ አረመኔ ቡድን መዳፍ መላቀቅ መቻል አለበት።በስሙ የሚነገድበት የኦሮሞ ተወላጅ በስሜ አትነግድ! ታሪኬን አታቆሽሽ!በአውሬነት እንድታይ አታድርገኝ! በኢትዮጵያዊነት የተጎዳሁና የኢትዮጵያ ጠላት አድርገህ አታቅርበኝ፣ኢትዮጵያ እኔና ሌሎቹ በጋራ ሆነን ያቆዬናት አገራችን ነች!አገሬ ኢትዮጵያ እንጂ የናንተ የፈጠራ ኦሮሚያ አይደለችም፣ኦሮሞ ቋንቋ መናገሬ የተለዬሁ አገር ዜጋ አያደርገኝም፤ቋንቋዬ ከሌላው የኢትዮጵያ ቋንቋ ጋር የተከላለሰ፣ባህሌም ከሌላው ባሕል ጋር የተወራረሰና የዳበረ፣ ጎሳዬ ከሌላው ጎሳ ተወላጅ ጋር ተዋልዶ ብዙ ማንነት ያለው እንጂ በነጠላው የቆመና ቆሞም ሊሄድ የማይችል ነው ብሎ ፊትለፊት መጋፈጥና ለእውነት መቆም አለበት።ለኢትዮጵያ ልዑላዊነት የተዋጉና የተሰዉትን የአድዋ ጀግኖች የሆኑትን የኦሮሞ ልጆች እነ ደጃዝማች ጎበና ዳጬ፣ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ(አባነፍሶ)ፊታውራሪ ገበዬሁ ጎራን እንዲሁም ከማይጨው ጦርነት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁኑ ትውልድ ድረስ ለኢትዮጵያ ክብር የተዋደቁትን ፤ጀነራል ጃጋማ ኬሎን፣ኮሎኔል አብዲሳ አጋን፣አቶ ይልማ ደሬሳን በሰሞኑም የሞቱት የካራማራውን ጀግና ሻለቃባሻ አሊ በርኬን፣በምሳሌነት እያቀረበ የነሱን ፈለግ በመከተል ታሪካዊ ድርሻውን ሊወጣ ይገባል።የሌላውም ጎሳ ተወላጆች የሆኑት ጀግኖቻችን የጉራጌው ፊታውራሪ ሃብተጊዮርጊስ የትግሬው ራስ አሉላ አባነጋ፣የአማራው ደጃዝማች በላይ ዘለቀና የመሳሰሉት በአድዋና በማይጨው ጦር ሜዳ ላይ ያደረጉት ተጋድሎ እኛን የአገር ባለቤት እንድንሆን አድርጎናል።

ስለኮሎኔል አብዲሳ አጋ ትንሽ ለማለት እንወዳለን።

ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከሆለታ ጦር ትምህርት ቤት በበታች ሹምነት ምሩቅ በመሆን ጣልያን ሲገባ በአርበኝነት የተዋጉ ናቸው።በጦር ሜዳ ስለቆሰሉ በሶማሊያ ወደብ በኩል ተግዘው በጣሊያን ለመታሰር ከተወሰዱት አርበኞች መካከል አንዱ ናቸው።ምንም እንኳን ምርኮኛ ቢሆኑም የጣልያን መንግሥት ጀግንነታቸውን አልካደም ነበር። ጣልያን ተሸንፋ እጇን ስትሰጥ አብዲሳ አጋና ሌሎቹ በክብር ወደ አገራቸው ለመመለስ በሮም ከተማ ለክብራቸው በተዘጋጀች ግልጽ የወታደር ጅፕ መኪና ሲጓዙ የኢትዮጵያን አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ሰንደቅ ዓላማ በጠላት መዲና በሮማ ያውለበለቡ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው።ከስደት ከተመለሱም በኋላ በተመደቡበት የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ጦር ወታደራዊ ግዳጃቸውን ፈጽመዋል፤በኮሪያ ጦርነትም የኢትዮጵያን ወታደራዊ ብቃት ያስመሰከሩ ፣የዓለም አቀፍ እውቅናና ሙገሳን የተቀዳጁ፣ ከፍተኛውን የጀግና ኒሻን የተሸለሙ ስማቸው ጎልቶ የወጣ ኢትዮጵያዊ መኮንን ናቸው።እኝህን ጀግና ኢትዮጵያዊ የኦሮሞ ማህበረሰብ ተወላጅ የመሰለ ሌላው የኤርትራ ተወላጅ ዘረዓይ ደረስም በሮማ ከተማ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በጠላት ጫማ ሲረገጥ አይቶ በመናደድ የጠላቱን ጎራዴ ነጥቆ የጣልያኖችን አንገት ቀንጥሶ ሕይወቱን ለአገሩ ክብር የሰጠ ጀግና ነው።ሌሎቹ የኤርትራ ተወላጆችም አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም አገራቸው በጣሊያን ወረራ በተያዘችበት ጊዜ በጦር አዛዡ በግራዚያኒ ላይ

ቦምብ ወርውረው ለመግደል ሞክረው ያልተሳካላቸው ጀግኖች ናቸው።ለኢትዮጵያ ክብር ከኤርትራ ከትግሬ፣፣ከኦሮሞ ፣ከሶማሌ፣ከአፋር፣ከአማራ፣ከጉራጌ ---ወዘተ የተውጣጡ ጀግኖች በከፈሉት ተጋድሎ ነጻነቷና አንድነቷ የተከበረችና ለእኛ ትውልድ ያለፈች ኢትዮጵያን እውን ያደረጉ ያገር ባለውለታዎች በተፈጠሩበት ቦታና ጎሳ በኋላ ላይ በተወለዱ አገር በቀል ባንዳና ከሃዲዎች አሁን ካለችበት ደረጃ ላይ መድረሷ ለወጡበት ጎሳ ብቻም ሳይሆን ለሰብአዊ ክብር ለሚቆመው ለመላው የዓለም ሕዝብ በተለይም ለአፍሪካውያን ሃፍረትና ቅሌት ነው።ለኢትዮጵያ ክብር፣ለአንድነቷና ለነጻነቷ የተሰዉት ጀግኖች አጽም  ይፋረዳቸዋል። የአሁኑም ትውልድ ያያት ቅድመ አያቶቹን መንፈስ ተከትሎ ለአገሩ ክብር፣ለነጻነቱና ለእኩልነቱ ብሎም ለወደፊቱ እጣፈንታው ሲል አሁን ያለውን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ መሳሪያ የሆነ፣ ጸረ ሰው፣ጸረ ሰላም፣ጸረ አንድነትና ኋላቀር የጎሰኞች ቡድንና ስርዓት ማሶገድ ይጠበቅበታል።

የመውደቂ ስጋት ያሰከረው የኦሮሙማው ቡድን የአጥፍቶ መጥፋት ዘመቻውን በሁሉም አቅጣጫ ተያይዞታል።ከአጋሩ ከወያኔ ቡድን ጋር በመሆን ለዓላማቸው እንቅፋት ይሆናል ብለው ባሰቡት ማህበረሰብ ፣በሃይማኖት ተቋማት፣በወጣቱ፣በምሑሩ፣በሠራተኛው መደብ፣በነጋዴው፣በሙያተኛው፣በአርሶ አደሩ፣በከተሜውና በገጠሬው ላይ ---ወዘተ አገር ለመበታተን ዓላማቸው ሲሉ  ያዘጋጁትን የወያኔና የኦነግ ጥምር ጦር በማዝመት በሁሉም አቅጣጫ የጥፋት ክንዳቸውን አንስተዋል።በዚያም ብዙ ንፁሃን ዜጎች ተጨፍጭፈዋል፣ቤተእምነቶች ወድመዋል፣ምእመናን፣መነኮሳት ህጻናት ሳይቀሩ በጥይት ተደብድበዋል። ወጣትነት ወንጀል ሆኖ በዬከተማው በዬመንደሩ ይሳደዳል፣ይታሰራል ፣ብዙዎቹ መድረሻቸውና መኖር አለመኖራቸው አልታወቀም።

የግፉ ዋንጫ ሞልቶ ያንገፈገፈው የአማራው ማህበረሰብ ለብዙ ጊዜ በተበታተነ መልኩ ሲያካሂድ የነበረውን  የፋኖ ትግል በአንድ አመራር ስር ለማካሄድ በመወሰኑ በጠላት መንደር ውስጥ ብርክ ወልዷል፤ያም ለጭካኔ እርምጃው መንስኤ ሆኗል።የሕዝቡ ትግል ይበልጥ እያደገና እዬጠነከረ ሲመጣ የስርዓቱም ያልሞት ባይ ተጋዳይ እርምጃ እንዲሁ እያደገ መምጣቱ አይቀሬ ነው።ያንን አውቆና ተገንዝቦ ይበልጥ መደራጀትና መሰባሰብ የግድ ይላል።በእስክንድር ነጋ የሚመራ የአማራው ብሔራዊ ግንባር  በዋናነት ለአማራው ደህንነት የተቋቋመ ቢሆንም መዳረሻውና የአማራውም ደህንነት የሚረጋገጠውና ዋስትና የሚኖረው የኢትዮጵያ መኖር ሲረጋገጥ በመሆኑ ለዚያ የጋራ ድል ሌሎቹንም ያቀፈ እንዲሆን ብዙ መሠራት ይኖርበታል።ሰርጎ ገቦች እንዳይጠልፉት መጠንቀቅ ተገቢ ነው። በምዕራባውያን በተለይም በአሜሪካኖች መዳፍ ውስጥ እንዳይገባ ብሔራዊ ልዑላዊነትን መርህ ያደረገ እንቅስቃሴ ሊሆን ይገባዋል።ያ ካልሆነ በውጭ አገር ሃይሎች የሚሽከረከር ቡድን ለሥልጣን ከበቃ የሚመጣው ለውጥ ሳይሆን የግለሰቦች የሥልጣን መቀባበል ይሆናል።ስለሆነም የውስጥና የውጭ ጠላትና ወዳጅን ጠንቅቆ የለዬ፣ታሪክን መሰረት ያደረገ በኢትዮጵያዊነት ፍልስፍና  የዳበረና የሚመራ ያገር ወዳዶች ስርዓት እንዲመጣ የሚያስችል ትግል  እንዲሆን የሌሎቹን ቀልብ ለመሳብና አመኔታ ለማግኘት ኢትዮጵያዊ  ገጽና ቁመና  ያለው የፖለቲካ

ድርጅት እንዲፈጠር ሁሉም የድርሻውን ማበርከት ይኖርበታል እንላለን።የአማራው ብሔራዊ ግንባር ለአማራው መብትና ህልውና የቆመ ሲሆን ለኢትዮጵያ አንድነትና ህልውና የሚቆም የሁሉንም ጎሳ ያካተተ ትግል የሚመራ የጋራ አመራር መፍጠር ለውጤቱ መሳካት ወሳኝ ነው።ምንም እንኳን የግለሰቦች አስተዋጽኦና ድርሻ የማይናቅ ቢሆንም ሕዝባዊ ትግሉ ለዘላቂና አስተማማኝ ለውጥና  ድል በግለሰቦች ትከሻ ላይ ብቻ ማረፍ የለበትም።ትግሉ መዋቅራዊ አደረጃጀት መያዝ ይኖርበታል።በግለሰቦች መኖር ወይም አለመኖር የሚወሰን ሳይሆን በድርጅታዊ የጋራ አመራር ከተመራ በመሪ እጦት ለክፍተት አይዳረግም።ግለሰቦችንም በተናጠል ለጥቃት እንዲጋለጡ አያደርግም።

ካለፉት ተደጋጋሚ ስህተቶች ተምሮ የግለሰቦች አምልኮ እንዳይኖር መከላከል ተገቢ ነው።ተቀምጠው የሰቀሉት ቆመው ለማውረድ እንደሚያዳግት ባለፉት ስርዓቶች ማለትም በደርግ፣በወያኔና በኦነግ መራሹ ብልጽግና አይተነዋል።ለወደፊቱም ሕዝባዊ ትግሉ የአንድ ጎሳ ተወላጆች በበላይነት የሚያሽከረክሩት፣ የግለሰቦች ዝናና ሥልጣን መጨበጫ እንዳይሆን  መጠንቀቅ ያሻል።የወደፊቱ ያገራችን ሥርዓት ከሰፈርና ከጎሳ ማንነት እንዲሁም ከቡድናዊነት የጸዳ በእውቀት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብና ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ እንዲሆን  ያስፈልጋል።መጀመሪያ ግን የአገር አንድነትና ህልውና ስለሆነ ለዚያ የፖለቲካ መስመር ወሳኝ ሊሆን አይገባም።ለመበታተን አደጋ የተጋለጠችውን አገሩን ለማዳን ቀኝም ሆነ ግራ ወይም መሃል ሰፋሪ  ያለውን ስርዓት ለማሶገድ ፍላጎት ያለው ሁሉ ሊሳተፍበት የሚችል ሰፊ መድረክ ሊሆን ይገባዋል።ይህ አይነቱ አደረጃጀትም ለሽግግር መንግሥቱ ምስረታ እንደ እርሾ እንደሚያገለግል ቀደም ባለው ጊዜ ያብራራነው ጉዳይ ሲሆን አሁንም ለመድገም እንወዳለን።

በደል የደረሰበት ማህበረሰብ ወይም ጎሳ  ለማንነቱ የመቆም መብቱ መከበር ሲኖርበት የጎሳ ማንነት ግን  የፖለቲካ መስመር ወይም ፍልስፍና ከሆነ እንደ ናዚዎች፣ ጽዮናዊነት፣ትግራዋይ/ተጋሩ ወይም ኦሮሙማ የፖለቲካ ፍልስፍና  የፈሽስቶች እንቅስቃሴ የመሆኑ ዕድሉ ከፍተኛ ነው።አማራነት፣ኦሮሞነት፣ትግራይነት፣ሶማሌነት፣አፋርነት---ወዘተ በኢትዮጵያ ውስጥ የማህበረሰብ የማንነት መለያ እንጂ የፖለቲካ ፍልስፍናና መመሪያ አይደለም።ሊሆንም አይገባም።የጎሳ ማንነት የፖለቲካ ፍልስፍና እንዳይሆን አጥብቆ መታገል ተገቢ ነው።ጎሳ በቋንቋና  ባህል ይገለጻል ፣ሃይማኖትና  የሚኖርበት ቦታ ብቸኛ መግለጫው አይሆንም።አማራ ሆኖ ኦርቶዶክስ ፣ሙስሊም፣ካቶሊክ፣ፕሮቴስታንት ወይም የሌላ እምነት ተከታይ ሊሆን ይችላል ነውም፣አማራ ሆኖ ወለጋ፣ትግራይ፣ኦጋዴን፣አፋር፣ጋምቤላ፣ደቡብ ---ወዘተ ሊኖር ይችላል፤ሌላውም እንዲሁ።የአንድ አገር ሕዝብ በሚኖርበት ቦታ የራሱን ቋንቋና ባሕል ይዞ መኖሩ እንግዳ ነገር አይደለም። ከሚኖርበት አካባቢም ከሚኖሩት ጋር የሚግባባበትን ቋንቋ ጨምሮበት ፣ባሕሉንም ተጋርቶ ይኖራል።በሁሉም የዓለም አገሮች የሚታዬው የሕዝብ ኑሮም ይህንኑ ያረጋግጣል።እኛ ኢትዮጵያውያን በምንኖርበት አገር ሁሉ በማንነታችንን፣ ቋንቋችንን፣ባሕላችንን፣እምነታችንን ይዘን የምንኖርበትን አገር ቋንቋና ባሕል ጨምረንበት

በሰላም እዬኖርን ነው።አገራችንም በዚህ መልኩ የኖረችበት ጊዜ አጭር አይደለም።አሁንም ሕዝቡ እዬኖረበት ነው።

አገራት በአንድ ብሔራዊ ቋንቋ መጠቀማቸውም አዲስ ነገር አይደለም።በታሪክ አጋጣሚ ብዙ ሕዝብ የሚናገረው፣ለስነጽሑፍ የሚመችና የራሱ ፊደል ያለውን ቋንቋ መያዙና መጠቀሙ ይመረጣል።አማርኛ ቋንቋም በጠባቦችና አገር በቀል ባንዳዎች ከቅኝ ገዥዎች ተግባር ጋር በማመሳሰል አማርኛን በሌላው ጎሳ ላይ የተጫነ ቋንቋ ነው በማለት ሲከሱ እራሳቸው ለውጭ ሃይሎች ወዶ አዳሪ በመሆን ለቋንቋቸው የአውሮፓውያኑን የላቲን ፊደል እንዲጠቀም በትውልዱ ላይ ሸክም ሲጥሉበት አላፈሩም።በዚህ የተውሶ የፈረንጆች ፊደል ለአጭር አረፍተነገር የሚሰፍረው ፊደል ብዛት፣ የሚወስደው ጊዜ፤ቀለምና ወረቀት ሲታሰብ ለደሃ አገር ሕዝብ ተጨማሪ ድካምና ኪሳራ ነው። እነሱ የተማሩበትና ለከፍተኛ ደረጃ የበቁበትን የአማርኛ ቋንቋ እንታገልለታለን የሚሉት ትውልድ እንዳይናገር አድርገውታል።እነሱ በመላ ኢትዮጵያ ተንቀሳቅሶ ለመኖር ሲችሉ ያልታደለው ትውልድ በጠባብ ሰፈር ውስጥ ተገድቦ እንዲርመሰመስ ፈርደውበታል።በአገራችን ሕዝብ ዘንድ ለጥቅም የዋለው አማርኛችን በተገለጹት መለኪያ መስፈርት እንጂ በበላይነትና በማስገደድ አይደለም።የሌሎቹም ቋንቋዎች እስከአሁን ድረስ ለመነገር የበቁት አማርኛ ቋንቋ ብቻ እንዲናገሩ አስገዳጅ ሁኔታ ስላልተጣለባቸው ነው።አማርኛ ቋንቋን የአንድ ጎሳ ማለትም የአማራው ብቻ አድርጎ ማዬት የቋንቋውን ስፋትና ተደራሽነት፣የሰጠውንም ጥቅም መካድና የአንድ ጎሳ ንብረት አድርጎ እራስን ከባለቤትነት ደረጃ ማውረድ ይሆናል።አማርኛ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ነው።የአማራው ጎሳ የኔብቻ ነው፤አትጠቀሙበት ብሎ የከለከለበት ጊዜም ታሪክም የለም።ያለውን በመስጠት የሌለውን በመቀበል የኖረ ሕዝብ ነው። በአገር ውስጥ አገር ጠሌዎቹ አማራውን ለማጥቃት ብሎም ኢትዮጵያን ለመበታተን ሲሉ አማርኛን ለማራከስና ከጥቅም ውጭ ለማድረግ ሲንደፋደፉ ይታያሉ።በሌላ በኩል የቋንቋውን ጥልቀትና ስፋት እንዲሁም ቃና ፣የፊደል ባለቤት በመሆኑም ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም የተረዱ ብሩህ አእምሮ ያላቸው የውጭ አገር ዩኒቨርሲቲዎችና የመንግሥት ተቋማት ሕዝባቸውን ለማስተማር ሰፊ እቅድ ዘርግተዋል፣ተማሪዎችንም አስመርቀዋል።

አሁን ያለንበት ሁኔታ

የስርዓቱ ግፍና በደል ከቀን ወደቀን እያደገ የመጣ ሲሆን የሕዝቡም ትግል በአንጻሩ እያደገ መጥቷል።የስርዓቱ ምንነት በሁሉም ዘንድ ታውቋል። ሁሉም የስርዓቱን መወገድ አጥብቆ ይሻል።ሃይማኖተኛው፣ፖለቲከኛው፣ሙያተኛው፣ነጋዴው፣አርሶ አደሩ፣ላብ አደሩ፣ከተሜው ፣ገጠሬው፣ወጣቱ፣አዛውንቱ፣ተማሪው፣አስተማሪው፣ጋዜጠኛው፣ኪነተኛው ሁሉም አንገፍግፎታል።በተናጠልም ቢሆን ተቃውሞውን በልዩ ልዩ መንገድ እዬገለጸ ነው።የቀረው ሁሉንም የሚያስተባብር አካል አለመኖሩ ብቻ ነው።ለዚያም ነው ብሔራዊ አስተባባሪ

መድረክ እንዲፈጠር በተደጋጋሚ ጥሪ የምናደርገው።አሁን ላይ እያደገ የመጣው የአማራው እምቢ ባይነት ነው።ይህንን እምቢባይነት ሌላውም ዜጋ ሊቀላቀለው ይገባል።

አማራው አገሩ ኢትዮጵያ ነች።የሚመራበት የትግል መርሆና መመሪያውም ኢትዮጵያዊነት ነው።ኢትዮጵያ ሲልም ብቻውን የሚቆጣጠራት አገር ትኑረኝ ብሎ ሳይሆን በውስጧ የሚኖሩት ዜጎች ጋር በህብረት፣በሰላም፣በፍቅር፣በመቀላቀልና በመስተጋብር ውህደት በእኩልነት የመኖር መብትን የማረጋገጥ ፍላጎት ያለው ሕዝብ መሆኑን የሚያሳይበት ትልቁ ማንነት ነው።ክልሌን ብሎ ዓላማውን በሰፈር አልከለለም። ለአማራው ኢትዮጵያዊነት ማለት የነጻነት፣የአልበገሬነት፣የጀግንነት መገለጫ ስለሆነ ያንን እንደ መመሪያ አክብሮና አስከብሮ ለመኖር ሲል መስዋእትነት ሲከፍል ኖሯል አሁንም እዬከፈለ ይገኛል።

የኦሮሙማውና የወያኔው አገር አጥፊው ጥምረት በበኩሉ የሞት የሽረት ትግል ለማድረግ ደፋቀና እያለ ነው።ወያኔ የወልቃይትንና የራያን ለም መሬት ለመንጠቅ አሰፍስፎ ይገኛል፣ኦሮሙማውም በበኩሉ የአማራውን አካባቢ በመውረር የተነሳውን እንቅስቃሴ ለመቅጨት ጦሩን አዝምቷል።መጭው ጊዜ ወሳኝ ሆኗል።ትግሉ በሕዝቡ ድል እንዲጠናቀቅ ሕዝባዊ እምቢተኝነቱ በሁሉም ያገሪቱ ክፍል በተለይም በከተማዎች መቀጣጠል ይኖርበታል።በተለይም የአዲስ አበባ ሕዝብ ትግል ወሳኝ ነው። ሙስሊሙ ፣ክርስቲያኑ እጅ ለእጅ ተያይዞ በእምነቱ ላይ የተዘጋጀውን አውዳሚ ዘመቻ ፊት ለፊት መጋፈጥ አለበት።ይህንን የጋራ ትግል ለጥቂቶች ብቻ በመተው ለጠላት መሳሪያ ከመሆን ሊታቀብ ይገባል።ቤቱ ሲፈርስ እያዩ፣ልጆቹ በጥይት ሲደበደቡ፣ ሲቆስሉና ሲታፈሱ እያዬ በዝምታ እድናለሁ ብሎ ማሰቡ ከሞት አያድነውም። ከተማዋን የከበበው አውሬ የኦነግ ጨፍጫፊ ቡድን ጭፍጨፋውን ከመጀመሩ በፊት ሕዝባዊ የመከላከል አቅም መገንባት አስፈላጊ ነው። ሰፈሮችን የሚጠብቅ ሕዝባዊ ዘብ ወይም ቃፊር ማደራጀት አንዱ የትግል አካል መሆን ይገባዋል።የንግድ እንቅስቃሴን መግታት፣የሥራ አድማ መምታት፣የከተማው ትግል አካል ነው። በማይረቡ የፖለቲካ ድርጅቶች፣በውጭ አገር ዲፕሎማቶችና በእምነት አባቶች ተማምኖ እጅን አጣጥፎ ለእልቂት መጋለጥ የለበትም።ለመብትና ለነጻነቱ ሕዝቡ በራሱ ተማምኖ ሊቆም ይገባል። እርስ በርስ መረዳዳት፣ለሚታገሉት ፋኖዎች ፣የስንቅና ትጥቅ ፣የሕክምና እርዳታ ማድረግ ለትግሉ ዋስትና ነው። በተጨማሪም መዘንጋት የሌለበት ለስርዓቱ ጉልበት የሆነው የአድርባዮቹና የሰላዮቹ መኖር ስለሆነ እነዚህን ደካማዎች ቢቻል መክሮ ከሚያደርጉት ተግባር እንዲቆጠቡ እምቢ ካሉም የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድባቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት ፣

ጠላትማ ምን ጊዜም ጠላት ነው፣

አስቀድሞ መምታት አሸክሿኪውን ነው።

የሚለውን ምክር ማስታውስና በተግባር መግለጽ ተገቢና አስፈላጊ ነው።

በገጠር የሚካሄደው ሕዝባዊ ትግል ቦታዎችን ከጠላት እዬነጠቀ ሕዝባዊ አስተዳደሮችን መመስረት ይገባዋል።የእራስ ገዝ ይዞታ ሳያጠናክሩ ጫካ ለጫካ መንከራተቱ ከድካም በቀር ብዙም ውጤት አያመጣም። የገጠሩና የከተማው ሕዝብ ትግል መናበብ አለበት።ለዚያ የሚረዱ በሚስጥር የግንኙነት መስመሮች መዘርጋት ይኖርባቸዋል።

ሥርዓቱ ውስጡን በከሳ ጸጉራማ በግ ወይም ሽንበቆ ይመሰላል።የውጭ አጋሮቹ የገንዘብ ድጋፋቸውን ነፍገውታል፣ የሙስና ብል በልቶታል፤እርስ በራሱ እዬተጫቃጨቀና እዬተባላ ነው።የቀረው ነገር ቢኖር የፕሮፓጋንዳው መሳሪያውና ገዳይ ክንፉ ብቻ ነው።ያም ቢሆን የሚቆይ አይሆንም።ለሠራተኛው በተለይም ለወታደሩ ደሞዝ መክፈል አቅቶት ዘርፎ እንዲበላ ፈቅዶለታል።ስርዓተ አልበኝነት ነግሷል።ንጹሃንን በማሰር የዋስትና ገንዘብ መጠዬቁን የገቢ ምንጭ አድርጎታል።በቤትና ንብረት ላይ የተጣለው መጠነ ብዙ ግብር ገንዘብ ለመዝረፍና መክፈል ያልቻለውንም ቦታውን ነጥቆ ለማባረር የታቀደ ሴራ መሆኑ አብዛኛው እዬተረዳው መጥቷል።አዲስ አበባን የማጽዳቱ አካል መሆኑም ተደርሶበታል።ለከተማው ነውጥ ሁሉም ሁኔታ ተሟልቷል የቀረው የተደራጀ አመራር ብቻ ነው።

የሙስሊም ወገኖቻችን ትግልም በጥሩ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ነው።ምንም እንኳን ተቋሙ በስርዓቱ ምንደኞች ቁጥጥር ስር ቢውልም ሰፊው ሙስሊም ከስርዓቱ ጋር ሆድና ጀርባ ከሆነ ቆይቷል።ባለፉት ሁለት ሳምንት ዓርብ ቀናቶች ለሶላት የወጣውን ሰላማዊ ሙስሊም የጨፈጨፈው የኦነግ ጨፍጫፊ በዚህም ሳምንት አርብ እለት እንደ ልማዱ ደም አፈሳለሁ ብሎ መስጊዶችን ከቦ በሱስ ሲቅበዘበዝ ውሏል።ሆኖም ግን ገዳይ ቡድኑ የለመደ የደም ግብሩን ሳያገኝ እንዲመለስ ሆኗል። የሙስሊሙ ማህበረሰብ በበሰለ ስልት በመስጊድ የሚያደርገውን የሶላት ጊዜ በቤቱ በማድረግ ከፈጣሪው ጋር ከመገናኘቱም በተጨማሪ ተቃውሞውን አሳይቷል።ለገዳዮች ጥይትም ሲሳይ ከመሆን ድኗል።የቤት ውስጥ ትግል ማለት እንዲህ ነው።ሁሉም በዬዘርፉ የሚሰማራው ከተሜ እንደሙስሊም ወገኖቻችን በቤቱ ቢቀመጥ ውጤቱ ትልቅ ነው።

ሌላው በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ በአገር ቤት የሚካሄደውን የኦሮሙማና የወያኔ ጥምር ሴራ በሚችለው መንገድ ማጋለጥና ለአገር ቤቱ የትግል አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል።የተያዘው ትግልና መሰባሰብ መልካም መሆኑ ቢታመንበትም በቂ አይደለም፤ይበልጥ መስፋትና ማደግ ይኖርበታል።በጎጥና በወንዜ ልጅተት አመለካከት እንዳይበከል መጠንቀቅ ተገቢ ነው።ለዚያም የተበታተነውና በልዩ ልዩ ስሞች የሚንቀሳቀሰው ስብስብ በአንድ የትግል ማእከልና የጋራ አመራር መመራት አለበት።ጠላቶቹ በአንድ አመራር በመመራታቸው ሊያጠቁ መቻላቸውን እንደ ምሳሌ ሊወስደው ይገባል።በውጭ አገር መንግሥታት መተማመኑንና አቤቱታውን ቀንሶ ሃይሉን በማጠናከሩ ላይ ቢያተኩር ይበልጥ ሊደመጥና ሊከበርም እንደሚችል ሊያውቀው ይገባል።

በጁላይ ወር በአውሮፓና በአሜሪካ የእስፖርትና የባሕል ዝግጅት በሚል ስም የሥርዓቱ ተጠሪዎችና ተባባሪዎች ሽርጉድ እያሉ ስለሆነ ምንም እንኳን እስፖርትና የባሕል ዝግጅቱ ለዘለቄታው መደረግ የለበትም የሚል አቋም ባይኖረንም እዬዬም ሲደላ ነውና አሁን አገራችንና ወገናችን ባሉበት የመከራ ጊዜ ላይ ዘፈንና እሸሸገዳሜ፣አስረሽ ምችው ድግስ የምናካሂድበት ጊዜ ነው አንልም።ጊዜው የብሔራዊ ሃዘን መግለጫችን (National mornning Period) ሊሆን ይገባዋል እንላለን።

በዝግጅቱ ቦታ ለመገኘት ያሰቡ የትግል አጋሮቻችን ወደ ልቦናቸው ተመልሰው በዚህ ቅጥ ያጣ፣የነጋዴዎች ድግስ ከመሳተፍ ይልቅ በሌላ ጊዜ እራሳቸውን ችለው በዬቦታው ዝግጅት ቢያደርጉ የሚመረጥና የተሻለ እንደሚሆንላቸው ማህበረሰቡንም የእኛ ነው በሚሉት ዝግጅት ማሰባሰቡ ለሞራላቸው ከፍታ እንደሚሰጥ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በዝግጅቱ ላይ በንግዱ ዙሪያ የሚሳተፉት አብዛኞቹ ከአገር ቤት የሚመጡ ወይም ከስርዓቱ ጋር ትስስር ያላቸው ነጋዴዎች ስለሆኑ በተዘዋዋሪ ለስርዓቱ የገንዘብ ምንጭ ከመሆን በዘለለም የአገሪቱን ገጽ የሚሸፍንና ለስርዓቱ ጭምብል ሆኖ የሚያገለግል መስሎ ይታዬናል።ስለሆነም ዝግጅቱ እንዳይሳካ ማድረግ ባለያም በዝግጅቱ ላይ አለመገኘት ተገቢ ነው እንላለን።

ለመልካም ውጤት፣ለአገራችን አንድነትና ነጻነት ለወገናችንም እኩልነት አብሮነትና ሰላም የሚከፈለውን ዋጋ ለመክፈል እንዘጋጅ።

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት| ለዘለዓለም ትኑር!